ወደኔ ተወዳጅ የሆነውና የትንሳኤ ቀንም መቀመጫው ወደኔ ቅርብ የሚሆነው መልካም ስነምግባር ያለው ነው።

ከጃቢር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው የአሏህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል፡ «"ወደኔ ተወዳጅ የሆነውና የትንሳኤ ቀንም መቀመጫው ወደኔ ቅርብ የሚሆነው መልካም ስነምግባር ያለው ነው። ወደኔ የተጠላውና የትንሳኤ ቀንም መቀመጫው ከኔ እጅግ የራቀው እውነትን ለመቀልበስ እየተጣጣረ የሚያወራ፤ ለአንደበተ ርቱእነት ንግግር የሚያበዛና ሙተፈይሂቆች ናቸው።" ሶሐቦችም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እውነትን ለመቀልበስ እየተጣጣረ የሚያወራንና ለአንደበተ ርቱዕነት ንግግር የሚያበዛን አውቀናል። መተፈይሂቆች እነማን ናቸው?" አሉ። እርሳቸውም "ኩራተኞች
ናቸው።" አሉ።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉ: ዱንያ ውስጥ ወደኔ ተወዳጁ፤ የትንሳኤ ቀንም መቀመጫው ወደኔ ቅርብ የሆነው ስነምግባሩ ያማረ ነው። ዱንያ ውስጥ ወደኔ የተጠላው የትንሳኤ ቀንም መቀመጫው ከኔ የራቀው መጥፎ ስነምግባር ያለው፤ (ሠርሣሮች) ከእውነት ለመውጣት ከአቅሙ በላይ እየተጣጣረ ንግግር የሚያበዛ፤ (ሙተሸዲቆች) ያለምንም ጥንቃቄ አንደበተ ርቱዕ ለመባልና ንግግሩን ለማላቅ ንግግሩን የሚያሰፋ፤ እና (ሙተፈይሂቆች) ናቸው። ሶሐቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! "ሠርሣሮች" እና "ሙተሸዲቆች"ን አውቀናል። "ሙተፈይሄቆች" ማን ናቸው? አሉ። እርሳቸውም: "ኩራተኞች፣ ንግግራቸውን በማስፋትና በንግግራቸው አፋቸውን በመክፈት በሰዎች ላይ የሚያፌዙ ናቸው።" አሉ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5802